## 1. አላማ

***ፆታዊ ትንኮሳ እና ከፆታ ጋር በተያያዘ በሚደረጉ አግባብነት የሌላቸው አቀራረቦች ለሰው ልጅ ክብር፣ ለሰው ነፃነት፣ ግላዊ ህይወት እና የፆታ እኩልነት ጐጂ ተግባራት ናቸው፡፡ የፆታዊ ትንኮሳ ድርጊቶች በተጨማሪም የወንጀል ድርጊቶተ፣ የዲሲፕሊን ግድፈቶች እና የገንዘብ ካሳ የሚያስጠይቁ ናቸው፡፡***

***ፆታዊ ትንኮሳ እና ከፆታ ጋር የተያያዘ አግባብነት የሌለው አቀራረብ በስራ ላይ ያለውን መልካም ግንኙነት የማያደናቅፍ እና በዚህ ህግ እና በዩኒቨርስቲው አግባብነት ያላቸው ህጐች መሰረት እንደ ዲሲፕሊን ጥሰት የሚታይ ሲሆን ከዩኒቨርስቲው ፖሊሲ ጋር ተፃራሪ እና ዩኒቨርስቲው የማይቀበላቸው ናቸው፡፡***

በዚሁ መሰረት ይህ ደንብ የሀይፋ ዩኒቨርስቲ ከፆታዊ ትንኮሳ ወይም ከፆታዊ ትንኮሳ የመነጨ አግባብነት የሌለው አቀራረብ ነፃ እና የተከበረ የስራ እና የትምህርት አካባቢ ሆኖ እንዲያገለግል ለማድረግ የታለመ ነው፡፡

## 2. <u>ትርጓሜዎች:</u>

| | |
|---|---|
| **“ዩኒቨርስቲ”** | የሀይፋ ዩኒቨርስቲ ማለት ነው፡፡ |
| ***“ህግ ማለት”*** | ከቁጥር 5758-1998 ያለው እና በዛ መሰረት የወጡ መመሪያዎች ፆታዊ ትንኮሳ ለመከላከል የወጣው ህግና ስለ ስራ ቦታ እኩል ተጠቃሚነት የሚደነግገው ቁጥር 5748-1988 ማለት ነው፡፡ |
| ***“ፆታዊ ትንኮሳ ማለት”*** | በክፍል 3(ሀ) ፆታዊን ትንኮሳን ለመከላከል በወጣው ህግና በስራ ቦታ እኩል ተጠቃሚነት ህግ አንቀፅ 7 ስር በተደነገገው መሰረት እና ከጊዜ ወደጊዜ በሚደረገው ማሻሻያ መሰረት እና በስራ ቦታ ላይ ሰራተኞችም ሆኑ ተማሪዎች እነዚህን ህጐች ለማክበር በሚያሳዩት ቁርጠኝነት መሰረት ማለት ነው፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው ጋር በማይፃረር መልኩ በህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ፆታዊ ትንኮሳ የሚያካትተው ከሚከተሉት አንዱን ባህሪ ነው፡፡ |
| | አንድን ሰው ፆታዊ ግንኙነት እንዲያደርግ ማስገደድ፡ ለምሳሌ፡- አንድን ግለሰብ ፆታዊ ግንኙነት አላደርግም በማለቱ ወይም በማለቷ ለማባረር መዛት |
| | አለአግባብ ማማለል - ለግብረስጋ ግንኙነት ፍላጐት መነሳሳት፣ እርካታ ወይም የስሜት መውረድ የሚያስከትል ድርጊት ለምሳሌ፡ ከእሷ ወይም ከእሱ ፈቃድ ውጪ አንድን ሰው ለወሲብ ፍላጐትን ለመቀስቀስ መነካካት በፆታ የተነሳ ፆታዊ በሆነ መንገድ የስልጣን ግንኙነትን አለአግባብ መጠቀም፡ እንዲህ አይነቱ የስልጣን ግንኙነት አለአግባብ መጠቀም |
| | (ለምሳሌ በፕሮፌሰር እና በተማሪው/ዋ); መካከል ሲፈጠር የፍላጐት ማጣትን ማመልከት አያስፈልግም፡፡ |
| | ተደጋጋሚ የፆታዊ ጥያቄዎች ተጠያቂው እንኳን ፍላጐት የማያሳይ መሆኑን ቢያመለክቱም; |
| | ስለ ግለሰቡ ሴሰኝነት በተደጋጋሚ መጥቀስ ምንም እንኳን ግለሰቡ ፍላጐት ባያሳይም ለምሳሌ ስለ ግለሰቡ አካላዊ አቋም በመጠቀም ከወሲብ ጋር ያለውን ነገር መጥቀስ ምንም እንኳን እንዲህ አይነቱ አገላለፅ እሷን ወይም እሱን የሚያሳስብ ቢሆንም፡፡ |
| | የእሷን ወይም የእሱን የፆታዊ ሁኔታ በሚያሳንስ ወይም ስሟን በሚያጠፋ አይነት መልኩ ማንሳት ምንም እንኳን እንዲህ አይነቱ ተግባር ግለሰቡን ቢያናድድም ባያናድድም በአንድ ግለሰብ ፆታዊ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ፎቶግራፍ፣ ፊልም ወይም ስእል ሲለጠፍ እና እንዲህ አይነቱን የተለጠፈ ነገር ግለሰቡን/ግለሰቧን የሚያሳፍር ሆኖ ሲገኝ እና እንዲህ አይነቱን ነገር እንዲታተም ወይም እንዲለጠፍ አይፈለግም፡፡ |
| | **የሚከተሉት ተግባራት እንደ *ፆታዊ* ትንኮሳ አይቆጠሩም**- አንድን ሰው በጥሩ መንፈስ በጋራ ፍላጐት እና በነፃ ፈቃድ ላይ በተመሰረተ <u>መጨዋወት ይህ ተግባር የስልጣን ግንኙነትን የማያሻክር ሆኖ ሲገኝ</u> |

| | |
|---|---|
| **"አግባብነት የሌለው አቀራረብ "** | ፆታዊ ትንኮሳን በወጣው ህግ ክፍል 3(ለ) መሰረት እና በስራ ቦታ አኩል ተጠቃሚነት ህግ ክፍል 7 ስር በተደነገገው መሰረት እና ከጊዜ ወደጊዜ በሚደረግባቸው ማሻሻያ እና ለውጥ በስራ ወይም በትምህርት ቦታ ሰራተኞች እና ተማሪዎች እነዚህን ህጐች ለማክበር በሚያሳዩት ቁርጠኝነት መሰረት፡- ከላይ የተቀመጠውን በማይገረር መልኩ በህጉ ድንጋጌ መሰረት የተከለከለ አግባብነት የሌለው አቀራረብ ማለት በሰራተኛ ወይም በስራ ፈላጊ ወይም በተማሪ ላይ በአሰሪ ወይም በአሰሪው ወኪል አማካኝነት ከፆታዊ ትንኮሳ በመነጨ ወይም ፆታዊ ትንኮሳ ላይ ባለ ቅሬታ የመነጨ ወይም አግባብነት ከሌለው አቀራረብ ከመነጨ ቅሬታ የሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ወይም ማንኛውም ከላይ የተጠቀሰውን ተግባር የፈፀመ ወይም እንዲፈፀም ያገዘ ወይም በፆታዊ ትንኮሳ ወይም አለአግባብ የሆነ አቀራረብ የቀረበ ቅሬታ ወይም ክስ ማለት ነው:: |
| **"ፈቃደኛ አለመሆን"** | ግለሰቦቹ የስልጣን ግንኙነት ከሌላቸው በስተቀር ቅሬታ አቅራቢው ተንኳሹ ግለሰብ በሚያሳየው ባህሪ፣ ቃላት ወይም ተግባራት ያልተስማማ/ያልተስማማች መሆኑን/መሆኗን ማመልከት አለበት/ባት |
| **"የአካዳሚ ስልጣን ግንኙነቶች"** | የአካዳሚ ስልጣን ግንኙነቶች የሚያካትቱት ቀጥታ ማስተማር (በመምህሩ ወይም በፕሮፌሰሩ በሚሰጥ የትምህርት ጊዜ / መልመጃ/ ላቦራቶሪ/ የቡድን እገዛ/የተግባር ትምህርት እገዛ/ላይ መሳተፍ);ጥናት የሚያካሂዱ ተማሪዎችን ማገዝ፣ ስኮላርሺፕ ማገዝ፣ የጥናት ስጦታ፣ የአካዳሚ ሽልማት ወይም ሌሎች ጥቅማጥቅሞች፣ በትምህርት ክፍል፣ በፋከልቲ ወይም በዩኒቨርስቲ ደረጃ ባሉ ኮሚቴዎች በተማሪዎች ጉዳይ ላይ በሚወያይ ወይም በማንኛውም አይነት መልኩ የተማሪውን የወደፊት እጣ ፈንታ ሊወስን በሚችል ነገር ላይ መሳተፍ:: |
| **"የስራ ወይም የትምህርት ቦታ"** | በዩኒቨርስቲው ውስጥ ወይም ሌላ ማንኛውም በዩኒቨርስቲው ቦታ ዩኒቨርስቲው ወይም ሌላ ማንኛውም ዩኒቨርስቲውን ተክቶ ለዩኒቨርስቲው ስራ ወይም ትምህርት የሚያከናውንበት ቦታ ማለት ነው:: |
| **"ተበዳይ"** | ማንኛውም ግለሰብ ሰራተኛ ወይም ተማሪ በስራ ወይም በትምህርት ቦታ ላይ በህጉ መሰረት የፆታዊ ትንኮሳ እና/ወይም አግባብነት የሌለው አቀራረብ ተጐጂ ሆንዋል ተብሎ የሚታመን ወይም የተገለፀ ማንኛውም ግለሰብ፣ ተማሪ ወይም ሰራተኛ ማለት ነው:: |
| **"ተከሳሽ"** | ክሱ በቀረበበት ቀን ወይም ድርጊቱ በተፈፀመበት ቀን የፆታዊ ትንኮሳ እና ወይም አለአግባብ የሆነ አቀራረብ በመፈፀም ክስ በህጉ መሰረት የቀረበበት ተማሪ ወይም ሰራተኛ ማለትነው:: |
| **"ኮሚሽነር"** | የፆታዊ ትንኮሳ ክሶች የሚቀርቡለት ኮሚሽነር ማለት ነው:: |
| **"ምክትል ኮሚሽነር"** | አግባብነት ያላቸው ባለስልጣናት ከኮሚሽነሩ ጋር ከተወያዩ በኋላ ከዚህ በታች ክፍል 4 ስር በተገለፀው መሰረት ሲሾሙ ማለት ነው:: |
| **"ሰራተኛ"** | ማለት ከፍተኛ የአካዳሚ ሰራተኞች፣ ጀማሪ የአካዳሚ ሰራተኞች፣ ጊዜያዊ ሰራተኞች ፣ ቋሚ ሰራተኞችን፣ በግል ኮንትራት ስር ያለ ሰራተኛ እና ማንኛውም በዩኒቨርስቲው ቦታ ሆኖ እየሰራ ያለ እና እንደ መደበኛ የውስጥ ስርአቱ በዩኒቨርስቲው ስም የሚሰሩ ለዩኒቨርስቲው አገልግሎት የሚያቀርቡ ድርጅቶች ወይም ሰራተኞቻቸውን ጨምሮ የሰራተኛ እና የአሰሪ ግንኙነት ከዩኒቨርስቲው ጋር ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ቀን ያለው ግለሰብ ማለት ነው:: |
| **"ተማሪ"** | ድርጊቱ በተፈፀመበት ቀን ከሚከተሉት አንዱን የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ማለት ነው:<br>- የልዩ አካዳሚ ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለዩኒቨርስቲው ማመልከቻ ያስገባ ወይም እንደ ተማሪው ዩኒቨርስቲው የተቀበለው ማመልከቻ ካስገባበት እና እንደተማሪ ከተመዘገበበት ወይም ከተመዘገበችበት ጊዜ ጀምሮ በአካዳሚ እረፍት ሰአትን ጨምሮ የዩኒቨርስቲው አመልካች ወይም ተማሪ ማለት ነው::<br>- ማመልከቻ ካስገባበት ጊዜ ጀምሮ የማመልከቻ መሻሪያ ደብዳቤ እስከደረሰው ጊዜ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በተማሪነት በዩኒቨርስቲው በተማሪነት ቅበላ እንዲደረግለት ያመለከተ እና የተከለከለ<br>- የተመረቀ ነገር ግን የመመረቂያ ዲፕሎማውን ያልወሰደ/ች |

**የ"ዲሲፕሊን ህግ"** ማለትም ፆታዊ ትንኮሳ ወይም አግባብነት የሌለው አቀራረብ ፈፅሟል በተባለ ግለሰብ ባለው/ላት ቀረቤታ ማለትም

- በሰራተኞች መብት ግዴታ መሰረት በሰራተኛ አባል በሆነ ተከሳሽ ላይ ተፈፃሚነት ያለው ህግ ማለት ነው፡፡
- ሰራተኛ በሆነ ተከሳሽ ላይ በአስተዳደራዊ ሰራተኞች ላይ ተፈፃሚነት ያለው የዲሲፕሊን ህግ ማለት ነው፡፡
- ተማሪ በሆነ ተከሳሽ ላይ ተፈፃሚነት ያለው የዲሲፕሊግ ህር ማለት ነው፡፡

**"የዲሲፕሊን ባለስልጣናት"** በዲሲፕሊን ህግ ሰነድ በእያንዳንዱ ውስጥ በተገለፀው መሰረት ይሆናል፡፡

**"ውሣኔ ሰጪ"** በፆታዊ ትንኮሳ ወይም አግባብነት የሌለው አቀራረብ ጉዳይ ላይ በተከሳሽ ላይ ባለው ቀረቤታ መሰረት ውሣኔ የማሰጥ አካል ማለት ነው:

- የከፍተኛ ወይም የጀማሪ የአካዳሚ ሰራተኞች አባል የሆነ እና ለከሳሹ ውሣኔ የሚሰጥ ሬክተር
- ተከሳሹ ሰራተኛ ከሆነ እና የከፍተኛ ወይም ጀማሪ የአካዳሚ ሰራተኞች አባል ሳይሆን ምክትል ዳይሬክተር
- ተከሳሹ ተማሪ ከሆነ የተማሪዎች ዲን

## 3. ፆታዊ ትንኮሳ እና አግባብነት የሌለው አቀራረብ እንደ ዲሲፕሊን ጥሰት የሚቆጠሩ የተከለከሉ ባህሪያት ናቸው፡፡

3.1 ፆታዊ ትንኮሳ እና አግባብነት የሌለው አቀራረብ በህጉ እና/ወይም በደንቡ በተሰጣቸው ትርጓሜ መሰረት የተከለከሉ እና አፀያፊ ተግባር ናቸው፡፡
የሚከተሉት ባህሪያት እንደዲሲፕሊን ጥሰት ይቆጠራሉ

3.2 **የአካዳሚ ስልጣን ግንኙነት ካለው አካል ጋር የቀረበ ግንኙነት መፍጠር**

3.2.1 በአካዳሚ ባለስልጣናት ግንኙነት መካከል አዋቂ ሰዎች በግል ስራቸው የስልጣን ግንኙነት ከሌላቸው የአካዳሚ ስልጣን ግንኙነትን ጨምሮ የሚካተቱ ሰዎች

3.2.2 በዚህ መሰረት ሁሉም የአካዳሚ ሰራተኞች አባላት ከፍተኛም ሆኑ ጀማሪ ሰራተኞች የአካዳሚ ስልጣን ግንኙነት ከፆታዊ አጋሩ ወይም አጋሯ ጋር የቀረበ ግንኙነት መፍጠር የለባቸውም፡፡

3.2.3 በተባለው መሰረት የቀረበ ግንኙነትን ለማስቀረት ከፍ ያለ የስልጣነ ደረጃ ላይ ያለው ወገን ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚህም መሰረት የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ጨምሮ ከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ላይ ያለው አካል ለእንደዚህ አይነት ግንኙነት ኃላፊነት ያለባት ሲሆን የምርመራ ችሎት ወይም የዲሲፕሊን ችሎት ላይ ቀርባ/ቦ የመጠየቅ ግዴታ አለበት፡፡

3.2.4 የቀረበ ግንኙነት በተባለው መሰረት መፈጠሩ የግድ ከሆነ የከፍተኛ ወይም ጀማሪ አካዳሚ ሰራተኞች አባላት ሁሉንም የአካዳሚ ስልጣን ግንኙነቶች ከተማሪ ጋር ማቋረጥ ወይም ለበላያቸው ሪፖርት ማድረግ እና ይህ የአካዳሚ ስልጣን ግንኙነታቸውን ማቋረጥ እና የተማሪውን ደህንነት ማስጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

3.2.5 ጥርጣሬን ለማስወገድ የከፍተኛ ወይም ጀማሪ የአካዳሚ ሰራተኛ ከራሱ/ሷ እና ቀደም ብሎ የቀረበ ግንኙነት ካለው/ተማሪ ጋር የነበረውን ግንኙነት ማስወገድ ይኖርበታል/ባታል የሚለው ግልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡

3.2.6 የአሁኑን ክፍል 3.2 መጣስ የዲሲፕሊን ጥሰት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

## 4. ኮሚሽነር ስለመሰየም:

4.1 የዩኒቨርስቲው ፕሬዝደንት እና ሬክተሩ ለተስማሙበት ጊዜ ኮሚሽነር የሚሾሙ ይሆናል፡፡

4.2 ኮሚሽነሩ በዩኒቨርስቲው የሙሉ ሰአት ፕሮፌሰር ወይም የትርፍ ሰአት ፕሮፌሰር ይሆናል፡፡

4.3 መደበኛ ፕሮፌሰር ከተፈለገ የከፍተኛ አካዳሚ ሰራተኞች አባል የሆኑ ሴት አባላት ይመረጣሉ::

4.4 ክህሎቱ እና ሙያዊ ልምዱ እንዲሁም የስልጣን ቦታው ለኮሚሽነርነት የሚመጥን ይመረጣል::

4.5 ኮሚሽነሩ በውሳኔው ገለልተኛ ነው::

4.6 ፕሬዝደንቱ እና ሬክተሩ ከኮሚሽነሩ ጋር ተመሳሳይ ለሆነ የሹመት ጊዜ ምክትል ኮሚሽነር ይሾማሉ::

4.7 ኮሚሽነሩ እና ምክትል ኮሚሽነሩ ከ18 ሰአት ላላነሰ ጊዜ የሚሰጥ ስለተሾሙበት ቦታ ስልጠና የሚወስዱ እና ስለተሾሙበት መደብ፣ በሀሪ፣ የህግ እውቀት፣ ቅሬታዎችን መከላከል እና ማስተናገድ ላይ እውቀት እንዲጨብጡ ይደረጋሉ::

## 5. የኮሚሽነሩ ሚና:

5.1 በዩኒቨርስቲው ውስጥ ፆታዊ ትንኮሳ እና አለአግባብ የሆነ አቀራረብን ለመከላከል እና ለማስተናገድ እንደአማካሪ ሆኖ መስራት

5.2 በፆታዊ ትንኮሳ እና አለአግባብ አቀራረብ ላይ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን እና ቅሬታዎች መቀበል::

5.3 በዚህ ደንብ ውስጥ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት ፆታዊ ትንኮሳ እና አለአግባብ አቀራረብ ላይ ምርመራ ማካሄድ::

5.4 በቀረበው ክስ ላይ የተደረገ ምርመራ ማጠቃለያ ከተብራራ የውሣኔ ኃሳብ ጋር ለውሣኔ ሰጪ ማስተላለፍ

5.5 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቅሬታ አቅራቢውን ለህክምና ወይም ለስነአእምሮ እርዳታ መምራት

5.6 በኮሚሽነሩ የስራ ጉዳይ ላይ በሚሰጡ ስልጠናዎች እና ድጋፎች ላይ በመደበኛነት እና በቀጣየነት መሳተፍ

5.7 በኮሚሽነሩ እና በምክትል ኮሚሽነሩ የስራ ይዘት ጉዳይ ላይ ሪፖርት ማቅረብ

5.8 በህጉ መሰረት ሚናውን/ናዋን ከግብ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነ ነገር በገዛ ስልጣኑ/ኗ ማንኛውንም ሌላ እርምጃ መውሰድ

## 6. የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ

6.2 ፆታዊ ትንኮሳ እና አለአግባብ አቀራረብ  ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ወዲያውኑ ድርጊቱ እንደተፈፀመ እንዲቀርብ ይመከራል:: ፆታዊ ትንኮሳ እና አለአግባብ አቀራረብ ከተፈፀመ በኋላ እስከ 7 አመት ድረስ ቅሬታ ሊቀርብበት ይችላል:: ድርጊቱን በተቻለ መጠን ጉዳዩን የሚያረጋግጡ ምስክሮች ( ማለትም ጓደኞች የቤተሰብ አባላት እንዲያስታውሱ ተደርጎ በሰነድ እንዲቀመጥ ይመከራል ).

## 7. *ፆታዊ ትንኮሳ ሲፈፀም የሚያስፈልጉ እርምጃዎች*

7.3 ህጉ የተለያዩ አማራጮችን የሚደነግግ ሲሆን የተወሰኑት ወይም ሁሉም አንድ ላይ ወይም ተራ በተራ ሊወሰዱ ይችላሉ::

7.3.1 አንድ ሰው በዩንቨርስቲው የፆታዊ ትንኮሳ መከላከል ኮሚሽነር ወይም በዩኒቨርስቲው አሰሪ የፆታዊ ትንኮሳ ክስ ሊያቀርብ ይችላል:: በዚህ ጊዜ የውስጥ የዲሲፕሊን እርምጃዎች መጀመር ይቻላል::

7.3.2 በስራ ግንኙነቶች ፍ/ቤት አንድ ሰው የፆታዊ ትንኮሳ ፈፃሚውን ወይም አለአግባብ የሆነ ባህሪ የሚያሳየውን ግለሰብ ሊከስ የሚችል ሲሆን አሰሪውን የገንዘብ ካሳ መጠየቅ ይችላል::

7.3.3 በሲቪል አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ለደረሰው ጉዳት አንድ ሰው ተንኳሹን ካሳ ለማስከፈል ሊከስ ይችላል::

7.3.4 የወንጀል ችሎት ለማሰየም ክስ ለፖሊስ ሊቀርብ ይችላል::

**8. በዩኒቨርስቲው ውስጥ የቅሬታዎች አያያዝ :**

**8.1 ጥያቄ:**

8.1.1 የፆታዊ ትንኮሳ ወይም አግባብነት የሌለው አቀራረብ ላይ ጥራጣሬ ኖሮ በሚቀርብ ክስ ወይም ቅሬታ በዩኒቨርስቲው ሲቀርብ ለኮሚሽኑ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ እንዲህ አይነቱ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም አግባብነት የሌለው አቀራረብ ከተፈፀመ እስከ ሰባት አመት ጊዜ ድረስ ለኮሚሽኑ ሊቀርብ የሚችል ሲሆን **ይህም ጉዳዩ ፆታዊ ትንኮሳን ወይም አለአግባብ አቀራረብን ያስከተለው ቆሞ ከሆነ ይሆናል፡፡**

8.1.2 ክሱ በቃል ወይም በፅሁፍ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ክስ የቀረበው በቃል ከሆነ ይዘቱን ኮሚሽኑ በፅሁፍ የሚመዘግብ ሲሆን ክስ አቅራቢው ወይም ክሱን ያቀረበው አካል ይዘቱን ለማረጋገጥ በፅሁፍ በሰፈረው አቤቱታ ላይ የሚፈርም ይሆናል፡፡ ኮሚሽኑ የተፈረመውን ኮፒ ለቅሬታ አቅራቢው ወይም ለፈረመው አካል የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የኮሚሽኑ ሰነዶች ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ እና ውስጣዊ ሆነው የሚያዙ ሲሆን ይግባኙን ለማስተናገድ ተብሎ ለውሣኔ ሰጪ አካል ካልተሰጠ በስተቀር ለሌላ ማንኛውም አካል ተላልፎ አይሰጥም፡፡

8.1.3 የፆታዊ ትንኮሳ ወይም አለአግባብ የሆነ አቀራረብ ጥርጣሬ ሪፖርት የቀረበለት ኮሚሽነር ወይም የፆታዊ ትንኮሳ ወይም አግባብነት ያለው አቀራረብ ክስ የተቀበለው ኮሚሽነር ክሱን ለማጣራት እና የምርመራ አካሄዶችን ለመግለፅ የክስ አቅራቢውን መብቶች እና በህጉ በተቀመጠው መሰረት ማድረግ ያለበትን ለማስረዳት ችሎት መሰየም ይኖርበታል፡፡

8.1.4 ኮሚሽኑ ክሱን በሚመረምርበት ጊዜ ተከሳሹን ጠርቶ ስለክሱ ዝርዝር ይዘት የሚያስረዳ እና መልስ እንዲሰጥበት የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ ተከሳሹ የተከሰሰው ድርጊቱ ተፈፀመብኝ ከሚል ግለሰብ ውጪ በሆነ ሌላ ሰው ከሆነ ተከሳሹ ኮሚሽኑ ተከሳሹን ከማነጋገሩ በፊት ባልተለመደ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በኮሚሽኑ የገዛ ስልጣን የተበዳዩ ፈቃድ ይጠየቃል፡፡

8.1.5 ክሱን ለመመርመር ኮሚሽኑ መረጃ ወይም ማንኛውንም ከክሱ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ሰነድ እንዲያቀርብለት ማንኛውንም ሰራተኛ ወይም ተማሪ ሊያስጠራ ይችላል፡፡ በህጉ መሰረት የተፈፀመ ካልሆነ በስተቀር ኮሚሽኑ ለጠየቀው ነገር ፈቃደኛ ለመሆን እንደዲሲፕሊን ጥሰት ይቆጠራል፡፡

8.1.6 ኮሚሽኑ ምርመራውን በአጥጋቢ ሁኔታ እስኪጠናቀቅ ድረስ በብቃት፣ በቀጣይነት እና ያለመዘግየት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

8.1.7 ኮሚሽኑ የጉዳዩ ልዩ ባህሪ እርዳታ የሚያስፈልገው ነው ብሎ ካመነ እራሱን ወይም እራሷን ለስነልቦና ባለሙያ፣ የማህበራዊ ሰራተኛ፣ የሰራተኞች አባል፣ የህግ ባለሙያ ፣ የቀድሞ ዳኛ ወዘተ በማማከር ያገኘውን ነገር ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

8.1.8 ክሱ የከሳሹን፣ የተበዳዩን፣ የተከሳሹን ወይም የሌሎች ምስክሮች ክብር እና የግል መብት በማይነካ መልኩ እንዲብራራ የሚደረግ ሲሆን በተለይ ኮሚሽኑ ክሱን በማብራራት ወቅት ያገኘውን መረጃ ክሱን ለማብራራት አላማ ካልሆነ በስተቀር ወይም በህጉ መሰረት አስገዳጅ ካልሆነ በስተቀር የሚያገኘውን መረጃ ይፋ ማድረግ የለበትም፡፡

8.1.9 ኮሚሽኑ መሀል ሰፋሪ መሆን እና እራሱን ከማንኛውም ክሱ የሚመለከተው ወገን ጋር ማገናኘት እና ድጋፍ መስጠት የለበትም፡፡

8.1.10 ኮሚሽኑ ተከሳሽ ከሆነ ወይም ከክሱ ጋር ወይም በክሱ ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች ጋር ማንኛውም የግል ትስስር ያለው ከሆነ ማንኛውንም ይግባኝ ወይም አቤቱታ ማስተናገድ አይችልም፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ኮሚሽኑ ለሚመለከተው ውሣኔ ሰጪ አካል ሪፖርት ማድረግ እና ክሱ ለጉዳዩ በተተኪነት በሚመረጥ አካል የሚመረመር ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ክሱ የሚመረመረው በዚህ ደንብ ውስጥ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

8.1.11 የውሸት ክስን በተመለከተ የሚቀርብ የውሸት አቤቱታ ወይም የውሸት ክስ ወይም በምንም አይነት መንገድ የውሸት ከሳሽን የሚደግፍ ሌላ ድርጊት የዲሲፕሊን ጥሰት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ክሱ የሚመለከታቸው ወገኖች በሚመለከታቸው ጉዳይ ላይ ኮሚሽኑ የክሱን ሂደት ያደናቅፈዋል ብሎ ካላመነ በስተቀር የሚቀርብባቸውን ማስረጃዎች የማየት መብት ይኖራቸዋል፡፡ ማንኛውም የምርመራ ሂደት ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ክሱ ለሚመለከተው አካል እንዲያይ ካልተደረጉ ኮሚሽኑ ይህንን በሪፖርቱ ውስጥ አካቱ የሚገልፅ ይሆናል፡፡

8.1.12 ዩኒቨርሲቲው ወይም ኮሚሽኑ በስራ ቦታ ወይም በትምህርት ቦታ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም አለአግባብ የሆነ አቀራረብ መከሰቱን ካወቀ እና ክስ ካልቀረበ ወይም ከሳሽ ክሱን ከተወ ጉዳዩ ለኮሚሽኑ እንዲመረምር የሚተላለፍ ይሆናል፡፡ ኮሚሽኑ ጉዳዩን በተቻለው መጠን መርምሮ ከላይ በተገለፁት ደንቦች መሰረት ከሳሽ ክሱን ከተወ ኮሚሽኑ ለምን እንደተወ ምክንያቱን የሚመረምር ይሆናል፡፡

8.2 በምርመራው መጨረሻ ላይ ኮሚሽኑ የክስ ምርመራ ማጠቃለያን ከቀጣይ የውሳኔ ሀሳብ ማብራሪያ ጋር ለውሳኔ ሰጪ አካል ያስተላልፋል

ተከሳሹ በዩኒቨርስቲው አገልግሎት ለማቅረብ በተቋራጭ የተገኘ ሰራተኛ ከሆነ የክሱ ኮሚሽነር የክሱን ማጠቃለያ እና የውሣኔ ኃሳብ አንድ ላይ አድርጐ ለሰው ኃይል አቅራቢ የሚያስተላልፍ ይሆናል፡፡

8.3 በየመሀሉ የሚወሰዱ እርምጃዎች

8.3.1 በክስ ምርመራ ወቅት አሰሪው ከሳሽ ክሱን በማቅረቡ ከሚደርስበት ሙያዊ አደጋ ወይም ጉዳት ወይም/ እና ማንኛውም በስራ ቦታ ወይም በትምህርት ቦታ ላይ የሚፈጠር ጉዳት ወይም የክሱን ሂደት የሚያደናቅፍ እንዳይደርስ የሚከላከል ይሆናል፡፡

8.3.2 በዚህም መሰረት እና እንደአስፈላጊነቱ ኮሚሽኑ ውሣኔ ሰጪ አካል በክሱ ሂደት ላይ ተከሳሽ እና ተበዳይ እንዳይገናኙ ማድረግን፣ ጊዜያዊ የስራ ኃላፊነት ለውጥ እና/ ወይም ወደሌላ የስራ ክፍል ማዛወርን ጨምሮ እርምጃ እንዲወስድ ይፈቅድለታል፡፡

8.3.3 በእንዲህ አይነት አልፎ አልፎ በሚያጋጥሙ በመሀል ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች ክሱ ከሚመለከታቸው አንደኛውን ወገን የሚጐዳ ወይም ፆታዊ ትንኮሳ እንዲቀጥል የሚያደርግ ሊሆን ይችላል፡፡

8.3.4 በሂደት ላይ የሚወሰድ እርምጃ የመጨረሻ ውሣኔ በውሣኔ ሰጪ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

8.3.5 የኮሚሽኑ ስልጣን እንደተባለው ክሱ እስኪመረመር እና ውሣኔ ሰጪ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ የተሰጠው ነው፡፡

8.4 የኮሚሽነሩን ማጠቃለያ እና የውሣኔ ኃሳብ ሲቀበል ውሣኔ ሰጪ አካል ኮሚሽኑ በተከታታይ 7 የስራ ቀናት ውስጥ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዛ በላይ የሆኑትን እንዲቀጥል ሊወስን ይችላል:

8.4.1 በጉዳዩ ላይ የተሳተፉትን መምከር አግባብነት ባለው በሀሪ ላይ ጨምሮ ምክር መስጠት

8.4.2 የስራ ቅጥር እና የትምህርትን ጊዜ የማያስተጓጉል ከሆነ ትንኮሳ አድርሷል የተባለውን አካል ከከሳሹ ማራቅ

8.4.3 ድርጊቱ ዳግም እንዳይፈጠር እና በከሳሹ ላይ የደረሰው ጉዳት እንዳይባባስ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ

8.4.4 የዲሲፕሊን ባለስልጣናት የክሱ ምልከታ እንዲቀጥል እንደአስፈላጊነቱ ክሱን ለዲሲፕሊን ባለስልጣናት ማቅረብ

**8.5 የውሣኔ ሰጪ ውሣኔ**

8.6 ውሣኔው የሚከተሉትን መረጃዎች የሚያካትት ይሆናል:

8.6.1 በሙያዊ እና /ወይም አካዳሚያዊ ግንኙነቶች ላይ አግባብነት ያለውን ባህሪ እስከመምከር ጨምሮ በጉዳዩ ለተሳተፉት ሰራተኞች ምክር መስጠት እና ተበዳዩን ከከሳሹ አርቆ ማቆየት፣ በሙያዊ እና ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ እርምጃ መውሰድ እና ክስተቱ ዳግም እንዳይፈጠር እና በተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት እንዳያገረሽ ማድረግ

8.6.2 በዩኒቨርስቲው አግባብነት ያለው የዲሲፕሊን ህግ መሰረት ፆታዊ ትንኮሳን በተመለከተ ከዚህ በታች በተገለፀው መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ችሎት ማስጀመር

8.6.3 ምንም አይነት እርምጃ አለመውሰድ

8.7 ውሣኔው የሚገለፅ ይሆናል

8.8 ውሣኔው ለከሳሽ እና ለተከሳሽ፣ ለኮሚሽነሩ እንደተብራራ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የኮሚሽነሩ ማጠቃለያ እና የውሣኔ ኃሳብ ማየት እስከፈለጉ ድረስ እነዚህን ሰነዶች ማየት ይፈቀድላቸዋል፡፡

8.9 ተከሳሽ በዩኒቨርስቲው ተቀጥሮ በተግባር ላይ ያለ ድርጅት ሰራተኛ ከሆነ የዩኒቨርስቲውን ውሣኔ ማን መስጠት እንዳለበት ውሣነ ሰጪው አካል ከተቀጣሪው ድርጅት ጋር ስምምነት ላይ የሚደርስ ይሆናል፡፡

8.10 ውሣኔ ሰጪው አካል ሁኔታዎች በመለወጣቸው ምክንያት ውሣኔውን ሊቀይር ወይም ስራውን ሊያቆምና ለከሳሽ፣ ለተከሳሽ እና ለኮሚሽነሩ የተብራራ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊልክ ይችላል፡፡

8.11 **በዚህ ውስጥ ያማይካተቱ ጉዳዮች**: ጉዳዩን ስጋት ላይ በሚጥል ምክንያት ውሣኔው ሊሻር፣ አፈፃፀሙ ሊዘገይ ወይም ሊቀየር ይችላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር ስለጉዳዩ ዝርዝር የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ለከሳሽ ተከሳሽ እና ኮሚሽነሩ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የተባለው ችሎት የሚቀጥል ከሆነ ዩኒቨርስቲው በክስ ሂደት ከሳሽ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ውሣኔ ሰጪው በክሱ ሂደት መጨረሻ ላይ ከላይ በተገለፁት ደንቦች መሰረት የሚሰጡ ይሆናል፡፡

## 9. የዲሲፕሊን ችሎት :

9.1 በተከሳሽ ላይ የዲሲፕሊን ክስ ሂደት ሲጀመር የክሱ ሂደት አግባብነት ባላቸው የዲሲፕሊን ደንቦች መሰረት መስተናገድ ይኖርበታል፡፡

9.2 በፆታዊ ትንኮሳ ወይም አግባብነት የሌለው አቀራረብ ክስ ጉዳይን የሚያዳምጥ ፖናል የተከሳሹን እና የተበዳዩን ፆታዊ አቋም በሚወክል አይነት መልኩ የተቀመጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

9.3 በዲሲፕሊን ክስ ሂደት ላይ ካሜራ ውይይት በካሜራ የሚቀዳ ይሆናል፡፡ በክስ ሂደቱ ላይ የታየ ማንኛውም ዝርዝር መረጃ ብይኑን ጨምሮ በተለየ መንገድ ፍ/ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር ሊታተም አይገባም፡፡

## 10. የትምህርት እና ለባለስልጣናት ይፋ የማድረግ እና ሪፖርት የማቅረብ ሁኔታ:

10.1 ዩኒቨርስቲው በአመት ቢያንስ አንድ ጊዜ በትምህርት ተግባራት ማለትም የጥናት ቀናትን፣ የቡድን ውይይት፣ በፆታዊ ትንኮሳ እና በመከላከያው ዙሪያ የመረጃ ቅፆችን በማሰራጨት ላይ ውይይት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

10.2 ዩኒቨርስቲው ለአዲስ ተማሪዎች እና ሰራተኞች የህጉን፣ የመመሪያውን የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

10.3 ዩኒቨርስቲው ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሪፖርቱም ዩኒቨርስቲው በራሱ ድንበር ውስጥ ፆታዊ ትንኮሳን ለመከላከል በአመት ውስጥ የወሰዳቸውን እርምጃዎች እና በአመቱ ውስጥ ለኮሚሽነሩ የቀረቡ እና የተስተናገዱ የክሶች ብዛትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

**11.ሚስጥር ስለመጠበቅ:**

ዩኒቨርስቲው በተቻለው መጠን እና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች እንደ ዩኒቨርስቲው የፆታዊ ጥቃት እና ትንኮሳን የመመርመር ግዴታ እና ኃላፊነት በሚወስዱት አካላት ላይ እርምጃ መውሰድ እና ፆታዊ ትንኮሳን ጨርሶ ለማስወገድ የጋራ እና የመከላከያ እርምጃዎችን እንደመውሰድ ያሉ ህጉ የሚያስቀምጣቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የከሳሹን፣ የተበዳዩን እና የተከሳሹን የግል መብት ማክበር ይኖርበታል፡፡

**12. የተሰበሰቡ ሰነዶችን ስለማስቀመጥ:**

በኮሚሽነሩ ለምርምራ የተያዙ ሰነዶች በዲሲፕሊን አስተዳደር ፍ/ቤት በሚያስቀምጧቸው ሰነዶች መሰረት የሚከማቹ ይሆናል፡፡

**13. የሚሾመው ኮሚሽነር :**

በዚህ ደንብ ውስጥ በተገለፀው መሰረት ዩኒቨርስቲው በዩኒቨርስትው ውስጥ ፆታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ለመከላከል ፕሮፌሰር ራኬል ሌቨል የቅሬታ ሰሚ ኮሚሽነር አድርጎ ሾምዋል

ፕሮፌሰር ራኬል ሌቭ በሚከተለው አድራሻ ይገኛሉ:

ፕሮፌሰር ራኬል ሌቭ፣ የስኩል ኦፍ አርት ቴራፒ ኃላፊ እና የስኩል ኦፍ ሶሻል ወርቅ ሰራተኛ አባል ናቸው፡፡

የስራ ስልካቸው.: 04-2822045

የሞባይል ስልካቸው.: 0528795849

ኢሜይል አድራሻቸው: RLEV@UNIV.HAIFA.AC.IL

በዚህ ደንብ ውስጥ በተገለፀው መሰረት ዩኒቨርስቲው በዩኒቨርስትው ውስጥ ፆታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ለመከላከል ማህበራዊ ሰራተኛ ኤሪስ ፌስለርን የቅሬታ ሰሚ ኮሚሽነር አድርጎ ሾምዋል

ማህበራዊ ሰራተኛ ኤሪስ ፌስለር በሚከተለው አድራሻ ይገኛሉ:

የስራ ስልክ: 04-8240608

የሞባይል ስልክ: 054-3213932

የኢሜይል አድራሻ: ifessler@univ.haifa.ac.il

በዚህ ደንብ ውስጥ በተገለፀው መሰረት ዩኒቨርስቲው በዩኒቨርስትው ውስጥ ፆታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ለመከላከል ዶ/ር ኒራ ፔንሰርን የቅሬታ ሰሚ ምክትል ኮሚሽነር አድርጎ ሾምዋል

የቅሬታ ሰሚ ምክትል ኮሚሽነሩ በሚከተለው አድራሻ ይገኛሉ:

ዶ/ር ኒራ ፔንሰር

የስራ ስልክ.: 04-8240914

የኢሜይል አድራሻ: nira@research.haifa.ac.il

አስባባሪ

ወ/ሮ ሻሮን ሲናይ

የስራ ስልክ .: 04-8240629

የተማሪዎች ህብረት ፀሀፊ

ወ/ሮ አሁቫ ሂያት

የስራ ስልክ: 054-2425233

የኢሜይል አድራሻ: ahiat@univ.haifa.ac.il

14. ይህ ደንብ ሲፀድቅ ተፈፃሚ የሚሆን እና ከዚህ በፊት በፆታዊ ትንኮሳ ላይ የነበሩ ህጐች እና ደንቦችን የሚተካ ይሆናል፡፡

15. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እና ሌሎች ማናቸውም ተፈፃሚነት ያላቸው የዲሲኘሊን ህጐች እና ደንቦች መካከል መጣረስ ካለ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የበላይነት ይኖራቸዋል፡፡

16. ይህ ደንብ በህግ እና መመሪያዎች ድንጋጌዎች ላይ ለመጨመር እንጂ ከነዚያ ውስጥ ለመሻር የታለመ አይደለም፡፡

17. **ኃላፊነት:**

17.1 የሰው ኃብት ዲፖርትመንት ኮሚሽነሮችን ይሾማል የሰራተኞች ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል

17.2 የተማሪዎች ዲን - የተማሪዎች ስልጠና እና ትምህርት

17.3 ኮሚሽነሮች ቅሬታዎችን ያስተናግዳሉ፡፡